## አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 10

ካለፈው ሳምንት ማጠቃለያ ተነስተን በቀጣዮቹ ቀናቶች የተከናወኑትንና የታዘብነውን ዋና ዋና ጉዳዮች ስንፈትሽ የሚከተሉትን ይመስላሉ።

ቀናቶች እንጂ ሁኔታዎች ሲለወጡ አልታዩም፤ዘንድሮም እንዳምናው፣ይህም ሳምንት እንዳለፈው ሳምንት የሕዝብ ብሶትና መከራ ይበልጥ እዬጨመረ የሄደበት እንጂ እዬቀነሰ አልመጣም።የጉሮ ውድነቱ፣ተስፋ ማጣቱ፣ስጋትና ጭንቀቱ፣መፈናቀሉ፣መገደሉ፣ዓይን ያወጣው የአንድ ጎሳ፣የኦሮሙማው የበላይነቱ ተጠናክሮ የወጣበት ሰሞን ነው።

ካለፈው ሳምንት ማጠቃለያ ስንነሳ ቅዳሜ እለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ 4ኛ ፓትሪያርክ የነበሩት የአቡነ ማርቆሪዮስ ስጋዊ እረፍታቸውን ተከትሎ በመስቀል አደባባይ የመሰናበቻ ስነሥርዓት ተከብሯል።በዚሁ ቀን ማታ ላይ የብልጽግና (ብልግና)ፓርቲ ድል ያለ ፌስታ አዘጋጅቶ ባለሥልጣኖቹ ጭፈራቸውን ሲያቀልጡት ታዝበናል።ምንም እንኳን ከብልጽግና ተብዬዎቹ ጸረ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ከሆኑት ጎራ የሞራል ልዕልና የሚጠበቅ ባይሆንም፣ሕዝብ በችግር በሚቆላበት፣በሚራብበት፣ በሚሰደድበት፣የእርዳታ ያለህ በሚልበት፣የኑሮ ውድነት መድረሻ ባሳጣበት፣እናት ለልጇ የደረቀ ጡቷን አጉርሳ የሰቆቃ ድምጽ በምታሰማበት፣ህጻኑ ዓይን ላይ የሞት ጣር ጥላውን በጣለበት፣ሁሉም ነገር በአስከፊ ግልባጩ በሚታይበት ወቅት በብዙ ሚሊዮን ብር ወጭ ያንን የመሰለ ድግስ መደገሱ መሪዎች ነን ባዮቹ ማንን እዬመሩ መሆናቸውን የተገነዘቡት አይመስልም።ቅብጠቱን ወንጀል የሚያደርገው ደግሞ የሥርዓቱ ሰለባ የሆነውን የአማራ ማህበረሰብ እንወክለዋለን ብለው ሥልጣን ላይ የወጡት ጉዶች ነጠላ አሸርጠው ሲጨፍሩና ሲቦርቁ ማዬት ነው።እነዚህ የኦሮሙማው ቡድን ምስለኔዎች እንኳንስእንወክለዋለን የሚሉት ሕዝብ ቀርቶ ዶሮም የታረደባቸው አይመስሉም።ዓይንና ህሊናቸውን የጥቅም መጋረጃ ሸፍኖታል።

በዋናነት ደግሞ ከ50% በላይ የሆነው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ተከታዬ በፓትሪያርኩ መሞት የደረሰበትን ሃዘን ሳይጽናና ብሎም የፓትሪያርኩ አስከሬን አፈር ሳይቀምስ ድል ያለ ግብዣ ማዘጋጀቱ ለእምነቱ ተከታዮችም ሆነ ለፓትሪያርኩ ክብር እንደሌለው ማሳያ ነው።ፓትሪያርኩ የአንድ እምነት መሪ ብቻ ሳይሆኑ የአገር ምልክት ነበሩ።ኦርቶዶክስ ተዋህዶን ከኢትዮጵያ ለይቶ ማዬት አይቻልም።ለኢትዮጵያ አገራዊ ቁመና፣ነጻነትና ክብር ቤተ ክህነት የድርሻዋን አበርክታለች።ወራሪ ጠላቶች፣የኢትዮጵያን አንድነትና ነጻነትም የማይሹ የውስጥና የውጭ ሃይሎች ሊያጠፏት የሚሞክሩትም ለዚያው አገራዊ ህልውና ባደረገችውና በምታደርገው ሰላማዊ ትግሏ ነው።ቤተክህነት በአገር ወዳዶቹ መንግሥታት ክብሯ ሳይደፈር ለመኖር ችላለች።ቀደም ፓትሪያርኮችን ክብራቸውን በሚገልጽ ደረጃና መልኩ ሸኝታለች።የቤተ ክህነት ውለታ የተረሳውና የማጥፋት ዘመቻ የተጀመረባት ከደርግ ስርዓት ጀምሮ ሲሆን ተጠናክሮ የቀጠለው ግን ባለፉት 30 ዓመታት ነው። በእምነቱ አባቶችና በምእመናኑ ያላሰለሰ ትግል አሁን ካለችበት ደረጃ ላይ ደርሳለች። የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክህነትም ሆነች ኢትዮጵያ በመኖርና ባለመኖር አደገኛ ጠርዝ ላይ ይገኛሉ።ሊገፏት ከተሰለፉት መካከል በሥልጣን ላይ ያለው ተረኛ ኦሮሙማው ጎሰኛ አገር አጥፊ ቡድን አንዱና ዋናው ነው።የብልጽግና ተብዬው ስብስብ በውስጡ 70% የሚሆኑት የፕሮቴስታንት ተከታዮች ሲሆኑ 20% ሙስሊም፣10% ኦርቶዶክሳውያን ናቸው።ታዲያ ለኦርቶዶክስ እምነትና አባቶች ክብር ቢነፈግ ምን ያስገርማል?ለዚያም ማሳያው በሃዘኑ ቀን ያደረገው አስረሽ ምችው ፌስታና ጭፈራ ነው። ጤነኛ መንግሥት ባለበት አገር ቢሆንማ ኖሮ ሌላው ቢቀር ከዜና እረፍታቸው ቀን ጀምሮ እስከቀብሩ ቀን ድረስ የብሔራዊ ሃዘን ሰሞን ተብሎ ይመደብ ነበር።

ዛሬ በኦርቶዶክስ እምነት ላይ የተሰነዘረ የጥቃት ዘመቻ ነገ በእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ ላለመከፈቱ ዋስትና የለም።አለመኖሩንም የተገደሉትን ሙስሊሞችና የተቃጠሉትን መስጊዶች ማሰቡ ይበቃል።የኦሮሙማው ቡድን የመጠቅለል ፍላጎት ሁሉንም በዬተራ አጭዶ እንደሚወቃ ከጅማሮው እስከአሁን ድረስ የሚያደርገውን የተረኝነት ጉዞ ማዬቱ ማረጋገጫ ነው።ካካሄዱ መረዳት ይቻላል። ከዚህ ጭፍን ዘመቻ እድናለሁ ብሎ የሚያስብ በጣም ጅላጅል ብቻ ነው።ሊድን የሚችለው በኢትዮጵያዊነቱ ተሰባስቦ ጸረ ኢትዮጵያ የሆነውን የጎሰኞች ቡድንና አስተሳሰቡን ሲያሶግድ ብቻ ነው። ሌላ አማራጭ የለም።

በፌስታና በእስክስታ ሲናጥ ያመሸው ብልጽግና በማግስቱ እሁድ ቀን ባደረገው የመጨረሻው ስብሰባ ሲጠበቅ የነበረው የድራማ ምርጫ ተከናውኗል።መራጩም፣ አስመራጩም፣ ተመራጩም አብይ አህመድ በሆነበት የምርጫ ድራማ በስክጀርባ አዘጋጅቶት በነበረው መልክ ውሳኔ አሳልፎ የሥራ ባልደረቦቹን መርጧል።በምርጫው ሂደት ላይ ብዙ አወዛጋቢ ድርጊቶችና ተንኮሎች የታዩበት ሲሆን ዓብይ አህመድና ቡድኖቹ የሚፈልጓቸውን በማስመረጥ፣የማይፈልጓቸውን ደግሞ በማባረር ጉልበታቸውን አሳይተውበታል።የተመረጡትም ሆኑ የተወረወሩት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሸክም እንጂ ሸክሙን የሚያቃልሉለት ስላልሆኑ በትዝብትና በንቀት ከመመልከት ባሻገር ለምን ብሎ የጠዬቀ የለም። ሊጠይቅም አይገባም።ሌሎቹንም የሚያነሳ ያንሳችሁ ብሎ ይመኛል እንጂ እንደ መልካም ለውጥ ቆጥሮ አያጨበጭብም።የሚያጨበጭበው የተረኝነቱን ቦታ ያረጋገጠውና ተላላኪ ምስለኔዎቹ ከነሆድ አደር ካድሬዎቹ ያሉበት ሰፈር ብቻ ነው። ሌላው ሰፊ ሕዝብማ

እግር ወዲያ ሄዶ እግር መጣ ወዲህ፣

እጅን የሚያወጣው እጅ ነው ከእንግዲህ።

ብሎ በትግሉ ለመቀጠል የወሰነበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ አድርጎታል።

ሞላጫው አብይ አህመድ በመዝጊያው ስብሰባ ላይ ስለ ፓትሪያርኩ አሸኛኘት ሲናገር "ሦስት ሆነን ሄደን ነበር አንድ ክርስቲያን የሚመስል ሙስሊምና ሁለት ሙስሊሞች"፣በማለት የራሱን ማንነት፣ ክርስቲያን መስሎ ማጭበርበሩን ሳያስበው አጋልጧል። አብይ ጴንጤ ነው እያልክ የምትደግፍ የጴንጤ ተከታይ የሆንክ ሁላ ሲጫወትብህና ሲጠቀምብህ እንደቆዬ ይህ የማያሳምንህ ከሆነ የምታምንበት አምላክ ልቦናህን ከፍቶ ያሳይህ እንላለን። አብይ ማጭበርበሩና መዋሸቱ አዲስ ስላልሆነ በዚህ ላይ ጊዜ ከማባከን ወደ ሌላው እርእስ እናመራለን።

በዛው እሁድ እለት ከተፈጠሩት ክንውኖች መካከል ካለፈው ሰሞን የቀጠለው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ግቢ የተካሄደው የጠባብ ጎሰኞቹ የኦነግ ቄሮ መንጋ በሌሎቹ በተለይም በአማራ ተማሪዎች ላይ የፈጸመው የጥቃት እርምጃ ነው።የአድዋ የድል በዓል ሲደርስ፣ባርነት ቀረብን ፣እንደሌሎቹ የቅኝ ግዛት ዜጎች በሰንሰለት ታስሮ ከመጎተት አዳነን፣ የነጻ አገር ዜጋ አደረገን ብለው ምንሊክን የሚወነጅሉት እነዚህ የኦነግ ፍልፍሎች ከመሰሎቻቸው የጥበቃ አባላት ጋር ተባብረው ብዙ ተማሪዎች ላይ ጉዳት አድርሰዋል።የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሲያዩ የሚያንቀጠቅጣቸው ዛራሞች ለጥቃት ያነሳሳቸው ለምን የምንሊክ ምስል ያለበት ካናቴራና አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ጥለት ያለበት ነጠላ ለበሳችሁ በማለት ነው።ከጥበቃ እስከ አለቃ የተመደቡት የዛው አገር ጠል ጎሳ ተወላጆች ከጽንፈኞቹ ጋር ተባብረው ጉዳት ከማድረስ በስተቀር ሕግ ለማስከበር አልሞከሩም።የዩኒቨርሲቲውም አስተዳደር ጥፋቱን በተጠቂዎቹ ላይ በመደፍደፍ የሚለብሱትን ልብስ እንዳይለብሱ አዟል። የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር እራሱ በሚመለምላቸው የጥበቃ አባላት ግቢውን ማስከበር ሲገባው በተረኝነት ባበደው አካል ትእዛዝ ሥር በወደቀ ቢሮ በኩል በመሆኑ የሌላ ጎሳ ተወላጅ የሆነውን ተማሪ ለጥቃት ያጋላጠው ዩኒቨርሲቲ

አስተዳደሩ ነው። የጎሳ ተረኛ የሆነው የቄሮ መንጋ ዛፍ ያለበት ባንዲራ ተሸክሞ ግቢውን ሲበጠብጥ ፤ የዛፍም ቅርንጫፍ ቆርጦ ዱላ አድርጎ የሰው ልጅ ሲደበድብ፣በድንጋይ ሲወግር ቅር አይላቸውም። ሥርዓቱም ከመደገፍ ባለፈ ድርጊቱን አልተቃወመም፤ወንጀለኞቹንም ተጠያቂ አላደረገም። ድርጊታቸውን ያዬ ሰው ከእንጨቱና ከድንጋዩ የተለዩ ፍጡር ናቸው ብሎ ለማመን ይቸገራል።

ለሚመጣው የትምህርት ዘመን ወደ ዩኒቨርሲቲ ከሚገቡት 152,000 ሽህ መካከል130,000 ሽ የሚሆኑት ከተረኞቹ ክልል መሆናቸው ታውቋል።ይህ ሁሉንም ቦታ ኦሮሞ የማድረግ ህሳቤ ለመሆኑ ሌለኛው ማረጋገጫ ሲሆን አብዛኛው ፈተና አልፎ ሳይሆን ተደጋግፎ የተለቀቀ መሆኑም ይፋ ወጥቶ እያነጋገረ ይገኛል።ሌላውን እንጎዳለን ሲሉ የራሳቸውን ጎሳ ተወላጅ ወጣት እውቀት አልባ አድርገው ሲጎዱት ማዬቱ መሪ ነን የሚሉት ሰዎች ህሊና ቢስ መሆናቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

በዛ የእውቀት መስክ፣የብሩህ አእምሮ ባለቤቶች መዋያ፣ከአገራቸው ከኢትዮጵያ አልፈው ለመላው አፍሪካ ብሎም ለዓለም ጭቁን ሕዝብ ድምጻቸውን ሲያሰሙና ሲታገሉ የነበሩ ቆራጦች በፈለቁበት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የጠባብ ጎሳ ማንነት የሚነዳቸው፣ከጅብ መንጋ ያልተለዩ ኂላ ቀሮች ሲፈነጩበት ማዬት የተማሪውን ብቻ ሳይሆን የትምህርቱንም ጥራትና ደረጃ ከጥያቄ ውስጥ ይጨምራል።ይህ በኦሮሞ ተማሪዎች በኩል የሚታዬው ሕገወጥና አውሬ ጸባይ የተረኛው ኦሮሙማ ቡድን ሁሉም ኬኛ በሚል ህሳቤ የሁሉም የሆነውን አዲስ አበባ ከተማን ለመዋጥ ስብጥሩን(ዴሞግራፊውን) ለመለወጥ ካለው ፍላጎት የመነጨ ነው።የከተማዋን ኦሮሞ ያልሆነ ነዋሪ ሕዝብ በሆነው ባልሆነው ሰበብ ተማሮ ከተማዋን ጥሎ እንዲወጣ ከሚደረገው ሴራ የተለዬ አይደለም።ነጋዴው በግብርና በቤት ኪራይ ጫና ንግዱን እንዲተው፣ሠራተኛው በቋንቋና በማንነቱ ምክንያት ከሥራው እንዲወገድ፣ነዋሪ ሕዝብ ከኖረበት ቦታው እንዲፈናቀል ማድረግ የሚደረገው ሴራ የዛው የኦሮሙማው ተስፋፊ ዓላማ አካል ነው። ማወቅ ያለባቸው ግን ማንም ቢሆን ከቆረቆረውና ከኖረበት ከተማ ንቅንቅ እንደማይል ነው። ዝምታው ከፍርሃት ወይም የነሱን እብደት በመቀበል መስሎ ከታያቸው ተሳስተዋል።የተነሳ ቀን ሜዳው ገደል እንደሚሆንባቸው ለመናገር የሚያምኑበት ጠንቋይ መሆን አይጠይቅም። በተለይም አማራውን መነካካት ምነው ባልጀመርኩት ያሰኛል።ከቆረጠ ሳይቆራርጥ አይመለስም።ሲጥል እንጂ ሲመታ አይታይም የሚባለውም ለዚያ ነው። ተከባብሮና በአንድ አገር ልጅነት መኖሩ ለሁሉም ይጠቅማል።ትውልድ መጥቶ ትውልድ ይሄዳል፤ታሪክና አገር ግን እዬተቀባበሉት የሚኖር የጋራ ሃብት ነው።መጥፎውን እያስገዱ መልካሙን እያሳደጉና እዬጨመሩበት መሄድ እንጂ ጥሩውን እያጠፉ በመጥፎ መተካት ሁሉንም ይጎዳል፤አገርን ያህል ትልቅ የጋራ ሃብት ለማፈራረስ መነሳት በራሱ ተተኪ ትውልድ ላይ መፍረድ ነው።አገረ ቢስ እንዲሆን ማድረግ ነው።አገር ቢፈርስ ሁሉም ተያይዞ ይፈርሳል እንጂ የሚተርፍ የለም። ትርፉ ተያይዞ መውደቅ ነው።የጦርነትንና የአገርን መፍረስ ጉዳቱን ያዩትን ማሰቡና መመልከቱ ከጥፋት ያድናል።ጤነኛ አእምሮ ያለው ከዚያ ይማራል።

የሚገርመው ነፍጠኛ በሚሏቸው መሪዎች አጼ ሃይለሥላሴ በስድስት ኪሎና አምስት ኪሎ በገነቡት ዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ ባይማሩም እዬዋሉ፣የሚቀርብላቸውን ድርጎ እዬበሉ፣ስማቸው ሲነሳ የሚያንቀጠቅጣቸው ዳግማዊ አጼ ምኒሊክ በአራት ኪሎ ባሠሩት ቤተመንግሥት ውስጥ እዬተንፈላሰሱ ዳውን ነፍጠኛ የሚል ጩኸት ሲያሰሙ ነፍጠኛ ከሚለው የጀግንነት ስያሜ ጋር በግብርም ሆነ በሃሳብ የሚዛመዱ ባይሆንም የዳውንን ትርጉም ባለማወቃቸው የእውቀት አልበኛነትን ብቻ ሳይሆን ጤንነታቸው ያጠራጥራል። ጤነኛና የሚያስብ አይምሮ ያለው ሰው ውለታ የዋሉለትን ያመሰግናል እንጂ ሲረግም አይኖርም። በጠባብነት ካንሰር እጢ የሚሰቃዩት እነዚህ የኦሮሙማ ጀሌዎች በጊዜው የሕክምና እርዳታ ያስፈልጋቸዋል እንላለን።መቼም ከዘመኑ ጋር የተጣሉ ናቸውና ዘመናዊ ሕክምና ያድናቸዋል ብለን አንጠብቅም። ሌላ የማህበረሰብ ባህላዊ መፍትሔ ከበሽታቸው ሲገላግላቸው

ይችላል ብለን እናምናለን።።በዋናነት ፋኖ የተባለው ወጊኛ ከተሸከሙት ዱላና ድንጊያ፣ካደረባቸው የጥላቻ ልክፍት ሊገላግላቸውና ሊፈውሳቸው ይችላል የሚል እምነት ስላለን በሽተኛ  ወገኖችን ጤነኛ ሰው ለማድረግ በሚደረገው ጥረት የከተማውና የገጠሩ ፣ሕዝባዊ ትግሉ ይፋፋም ዘንድ ሁሉም የድርሻውን ያበረክት ዘንድ ጥሪ እናደርጋለን።

የኦሮሙማው መንፈስ የሚነዳው የቄሮ መንጋ ያለበትን የእብደት ደረጃ የሚያሳየውን በጎሳ ማንነታቸው ምክንያት ጥቃት የደረሰባቸው ተማሪዎች የሰጡትን ማብራሪያና በዩኒቨርሲቲው የተፈጸመውን አሳፋሪ ድርጊት የሚያሳዬውን የድምጽና የምስል ማስረጃ በሚከተለው የዩቲዩብ ስርጭት መረዳት ይቻላል።

https://youtu.be/07TUCrnfm1M

https://youtu.be/1tWoHPRCJXg

ወደ ሌላው የሰሞንኛው ትችታችን ስናመራ ቅድሚያና ሰፊ ትኩረት የተሰጠው የአማራውን ልዩ ሃይልና ፋኖን ለማጥፋት የብልጽግና ቡድን የወሰደውና እዬወሰደ ያለውን እርምጃ የሚመለከት ይሆናል። በተለያዩ ጊዜያቶች ሙከራ ሲያደርግ የቆዬው ብልጽግና  በተለያዩ አካባቢዎች ለአገሪቱ ሰላምና ለሕዝቡ መብትና ደህንነት የሚታገሉትን የአማራ ፋኖና ልዩ ሃይል አባላት ለማፈን ብሎም ለማጥፋት ከምን ጊዜውም በበለጠ ዝግጅት አድርጎ  እዬተንቀሳቀሰ ይገኛል።የነዚህ ሕዝባዊ ሃይሎች መኖር ያሰበውን አገር የማፈራረስ ዓላማው እንቅፋት ከመሆናቸውም በላይ ለባእዳን ሸጦ ገንዘብ እሰበስብበታለሁ ያለውን የአማራውን መሬት፣በተለይም ወልቃይትን ለመቀራመት ያለው ዓላማ ግቡን ስለማይመታ የግድ የሕዝባዊ ሃይሉን ማዳከም ብሎም ማጥፋት የመጀመሪያውና የመጨረሻው እርምጃ አድርጎታል።

ይህ ነውረኛ ቡድን ወያኔ ይከተለው በነበረው የከባቢው የማንነት ጥያቄ በሕዝበ ውሳኔ ይፈታል ሲልም ተደምጧል።ሕዝበ ውሳኔ ማለቱም የቀድሞ ነዋሪው ተገሎና ተፈናቅሎ በመመናመኑ በቦታው መጥቶ የሰፈረውን የትግራይ ሰፋሪ ብዛት በመተማመን ነው።ከሦስት ዓመት ወዲህ ግን በትግሉ ወደ ታሪካዊ ባለቤቱ በሆነው የአማራ ተወላጅ ቁጥጥር ሥር በመዋሉ ሊዋጥላቸው አልቻለም።ነዋሪውን በተንኮልና በገንዘብ ለመደለል ያደረጉት ሙከራም አልተሳካም።ስለሆነም ያላቸው አማራጭ በሃይል ማንበርከክና መሬቱን መንጠቅ ስለሆነ ከወያኔና ከሱዳን ወራሪ ሃይል ጋር በመተባበር በአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ ላይ ጉዳት እያደረሱ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል። ትግሉ በመኖርና ባለመኖር፣የሞትና የሽረት ትግል ነው።ስለሆነም አማራው ለአንዴና ለሁለዬው የወልቃይትን መሬት አስከብሮ ለመኖር ከሚያደርገው ትግል ያፈገፍጋል ተብሎ አይጠበቅም።ትግሉ የመሬት ብቻ አይደለም፤ትግሉ የማንነትና የዜግነት መብት ማስከበርን የሚመለከት ነው።ስደትና ውርደትን ከመጠዬፍ የመነጨ አገር ወዳድነትን የሚያበስር ትግል ነው።

በሰሜን ወሎ የራያ፣አዘቦና አበርገሌ ከባቢ በወያኔ ቁጥጥር ሥር እንዲወድቅ ማድረጉም የመንግሥት ተብዬውን ቡድን የተቀናጀ ሴራ መሆኑን ዝምታው ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።ወያኔ ዳግም አንሰራርቶ በአማራውና በአፋሩ መኖሪያ ላይ የወረራ ብትሩን ሲያሳርፍ በዝምታ ያለፈው መከላከያ ተብዬው የሥርዓቱ ክብር ዘበኛ እጁን አጣጥፎ ከማዬት ባሻገር ለተቀጠረበት ሙያና ለሚተዳደርበት ደመወዝ ከፋይ ለሆነው ሕዝብ ጥሪ ደንታ ቢስ መሆኑ በተረኝነቱ ገመድ መተብተቡን ያመላክታል።

ደግመን ደጋግመን እንዳሳሰብነው አሁንም ሳንሰለች ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚከተለውን ጥሪ እናቀርባለን።ላለፉት ሃምሳ ዓመታት ማንነትህን በቋንቋና በምትከተለው ሃይማኖት ፈርጆ የአገር ባለቤትነትህን ነፍጎ እንደ እንስሳ በክልል ወጋግራ አጥር ውስጥ የከለለህ ስርዓት፣ የጎሳ ፖለቲካና በጎሰኞቹ የተቀረጸው መመሪያ (ሕገ-መንግሥት) ስለሆነ ይህንን አሽቀንጥረህ ካልጣልክ በስተቀር እንደ

ሰውና እንደ ዜጋ ተከብረህ፣የአገር ባለቤት ሆነህ ለመኖር እንደማትችል ተረዳ።ባለፉት ብዙ ዓመታት አያሌ መስዋእትነት ከፍለሃል።ታርደሃል፣ተፈናቅለሃል፣ታስረሃል፣ ተሰደሃል።ልጆችህም ከዚያ የተሻለ እጣ ፈንታ አልገጠማቸውም።

በስምህ የሚነግዱ ከራስህ አብራክ የወጡ ከሃዲዎችም ለመጠቃትህ ተባባሪዎች ናቸው።አንተን ቢመስሉም አንተን መሆን አልቻሉም።ይባስ ብለው ሊያጠፉህ ከሚያሴሩት ጠላቶችህ የበለጡ ጠላቶች የሆኑት እንሱ ናቸው።ለጥቅም ያደሩትን እዬመለመሉ የሚያዘምቱብህ  እነዚሁ  ከሃድያን ናቸው። እስከመቼ ልጆችህን እዬገበርክ፣ተሰደህ፣ተፈናቅለህና እንደ በግ ታርደህ ትኖራለህ?እስከመቼስ በስምህ ለሚነግዱት ሆዳምና ባንዳዎች መጠቀሚያ ትሆናለህ?

ያለህ አማራጭ አንድና አንድ ብቻ ነው።ያም እጅ ለእጅ ተያይዘህ ጠላቶችህ በመጡበት መንገድ ሄደህ አገርህንና እራስህን ማዳን ብቻ ነው።በተዝረከረከና በተበታተነ መልኩ ልትቋቋመው የምትችለው አደጋም ስላልሆነ በመካከልህ ያለውን ጥቃቅን ልዩነት አሶግደህ በአድዋው መንፈስ አንድ ሆነህ ለፍልሚያው መሰለፍ ነው።ለትግል መሪ ስለሚያስፈልገውም በአንድ ነጠላ ግለሰብ ሳይሆን በተቀናጀ መልኩ የሚመራ የጋራ አመራር መፍጠር አስፈላጊና ወሳኝ ነው።አንተ ተደራጅተህ ስትገኝ ሌላው ይከተልሃል፣እኛም አብረንህ እንሰለፋለን።

በውጭ አገር የምትኖረው አገር ወዳዱ ኢትዮጵያዊ ሆይ! ለአገርህና ለወገንህ ሳትሰለች የምትችለውን አበርክተሃል፤አሁንም እያበረከትክ ነው።ሆኖም ግን ድካምህ የሚፈለገውን ፍሬ አላፈራም።ለምን ብትል በአገር ፍቅር ስሜት ብቻ በመነዳት በዬጊዜው አለን ብለው በሚነሱ ቡድኖችና  ግለሰቦች ላይ  እምነት ጥለህ በመገኘትህ ነው።እነዚያ እምነት የጣልክባቸው የት ላይ እንዳሉ የምታውቀው ስለሆነ እዚህ ላይ ማንሳቱ አላስፈላጊ ነው።ትምህርት ያገኘህም ይመስለናል።ትምህርቱም ከቡድንና  ከግለሰብ አምልኮ ተላቆ ሕብረ ብሔራዊና ኢትዮጵያዊ ቁመና ያለው ሕብረ ብሔራዊ ትግል ለማካሄድ የሚችል የተውጣጣ ሕዝባዊ የጋራ  አመራር መፍጠር እንዳለብህ የሚያሳስብህ  ነው። ይህ የጋራ አመራሩ በፖለቲካው፣በኤኮኖሚው፣በወታደራዊው፣በማህበራዊው ጉዳዮች ላይ ፈጣንና ትክክለኛ መልስ የሚሰጥ ይሆናል። ጠላቶችህ በነዚህ ዘርፎች ከአንተ በተሻለ መልክ የተደራጁ ናቸው።ከአንተ የተሻለ እውቀትና ወኔ ኖሯቸው ሳይሆን ለቆሙለት የጥፋት ዓላማ መቁረጣቸውና  መናበብ መቻላቸው ነው።

ጥቂት ሰዎች ለጠባብና  ለጥፋት ዓላማ ሲተባበሩ እንዴት ብዙሃኑ ሊጠቀምበት ለሚችለው ለጥሩ ብሎም አገራዊ  ዓላማ አይተባበርም?የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴት ለሰፈርተኛ አሸባሪ ቡድን ይንበረከካል? እንዴትስ ብሎ ሥልጣኑን ለነጠቁት የአሸባሪዎቹ  አካል በሆኑ ጥቂት አጭበርባሪዎች ተታሎ ይኖራል?በብልጽግና ተብዬው የጥፋት ሃይል ተታሎ እምነት ጥሎ መቀመጥ ማለት የሚታነቁበትን ገመድ አዘጋጅቶ የመስጠት ያህል ነው።

ዘፈንና ፉከራ በተወሰነ ደረጃ መልካም ቢሆንም፣በመቀስቀሻና በማስተማሪያነቱ የሚሰጠው ጥቅም እንዳለ ባይካድም፣ትግሉ በእስክስታና ጭፈራ ይጠናቀቃል፣ግቡንም ይመታል ማለት አይደለም። ፉከራው በተግባር መተርጎም ይኖርበታል።ቀደም ሲል ፋኖ ተሰማራ እያለ የዘመረው ትውልድ ፋኖነቱን በከተማና በገጠር አሳይቷል።ምንም እንኳን በገጠመው ውስጣዊና ውጫዊ ችግር ምክንያት ካሰበው ባይደርስም ወጣቱን ትውልድ ከአድርባይነትና ከፍርሃት ነጻ አድርጎታል።ፋኖነት ከኢትዮጵያውያን ታሪክና ነጻነት ጋር አብሮ የኖረ፣ከደምና ከአጥንቱ ጋር የተቆራኘ የጀግንነቱ ምልክት ነው።አሁንም ፋኖነት እንደ ድንገተኛ ጎርፍ  ሳያስቡት የሚመጣ ሳይሆን  በጀግና ሕዝብ ሰውነት ውስጥ የሚንተከተክ ስሜት የሚረጨው ወኔ ነው።የዚያ ባለቤት የሆነ ሕዝብ እንደ አያት ቅድመ አያቶቹ እምቢ ላገሬ! እምቢ ለሙብቴና ለነጻነቴ ብሎ መሰለፍ ይጠበቅበታል። ያም በመታዬት ላይ ነው።የአማራ ፋኖ

መነሳትና የአማራ ልዩ ሃይል መፈጠር ከቀድሞው የቀጠለ እንጂ ዱብ እዳ አይደለም። የአሁኑ ትውልድ የተረከበውን አገር ለቀጣዩ ትውልድ የማስረከብ አላፊነትና አደራ አለበት።

በማልቀስና በመጮህ፣ለአስለቃሾቹ ይግባኝና ልመና በማቅረብም መፍትሔ አይገኝም።ሕዝብ ባለቀሰ ቁጥር አስለቃሾቹ ይረካሉ፣ይበልጥ ለማስለቀስም ይጥራሉ። መፍትሔው በአንድነት፣ለአንድነት መቆምና አስለቃሾቹን ማሶገድ  ብቻ ነው። ለዚያም ሕዝባዊ ትግሉን በከተማና በገጠር ማካሄድ ብቻ ነው። ሕዝብ ያሸንፋል እንጂ አይሸነፍም።ለጊዜው ባልታሰቡ ድክመቶች ሊጠቃ ቢችልም እንኳን የኋላኋላ ትግሉ በሕዝብ አሸናፊነት ይጠናቀቃል።ለጊዜው ሊሸነፍባቸው የሚችልባቸው ደካማና ስስ ጎኖች ካሉ ማረምና ማስተካከል ለስኬቱ ዋስትና  ነው።በአዋቂዎች ስብስብ  የሚመራ ትግል ከድክመቱ ይልቅ ጥንካሬው ያመዝናል።አዋቂዎች ሲባልም ድግሪ ያነገበ ምሑር ብቻ ነው ማለት ሳይሆን አገሩን፣ታሪኩን ባህሉን፣እምነቱን፣የሚያውቅ በስነ ምግባር ታንጾ  ያደገውን ሰው የሆነ አገር ወዳድ ማለታችን ነው።

በአጠቃላይ አገራችን በቀውስ ውስጥ መናጧን ማመን ለቀጣዩ ትግል መነሻ እርከን ይሆናል።ሽፋፍኖ ማለፍ እራስን ማታለል ብቻ ሳይሆን  ተተኪ ትውልዱንም ማታለል ነው።

በመሬት ላይ ያለውን ስንመረምር እንደሚከተለው ነው።

1/ ወያኔ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ተዘጋጅቶ ዳግም ወረራ ለማካሄድ በመንቀሳቀስ ላይ ነው።የወሎን ሰሜን ክፍል ተቆጣጥሮ  ሕዝቡን በራሱ ሕግ እያስተዳደረና የሚፈልገውን እዬሰበሰበ ይገኛል።

2/ በአፋር በኩል ጥቃቱን አስፋፍቶ መጠነ ሰፊ ጉዳት አድርሷል፤ያልያዘውን ቦታ ለመያዝም ብዙ ጦር አሰልፏል።የአፋር ሕዝብ በተደጋጋሚ ላቀረበው የድረሱልኝ ጥሪ መንግሥት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሏል። ብቻውን እዬተፋለመ ነው።

3/  በኤርትራም በኩል እንዲሁ ጥቃት ለመሰንዘር ያላሰለሰ ሙከራ አድርጓል።የኤርትራ መንግሥት ግን የሚቻል አልሆነበትም።እንደ እብድ ውሻ የሚዋከበው ወያኔ ከኦነግና ከመሰሎቹ የሽብር ቡድኖች በተጨማሪ የኢትዮጵያ መንግሥት ነኝ ባዩም ቡድን የስውር እጅ እንዳለበት ብዙ አመላካቾች ታይተዋል።ሰላምና እርቅ በሚሉ ሽፋን የወያኔን ጥያቄ ለመመለስ ዳር ዳር ማለቱና ለሚወስደው ጥቃት ተገቢ ምላሽ አለመስጠቱ አንዱ ማሳያ ነው።

4/ በአዲስ አበባ ወጣቶች ላይ የተጀመረው የማሳደድና የማሰር ዘመቻ ተፋፍሟል።የታሠሩትም በአባ ሳሙኤል በሚባለው የኦሮሚያ ከባቢ ባለው እስር ቤት ውስጥ ስቃይ እያዩ ነው።ንጽሕና በሌለው እስርቤት ውስጥ ምግብና ውሃ ከለማግኘታቸው የተነሳ ለብዙ በሽታ ተጋልጠዋል።የህክምና እርዳታም ተነፍጓቸዋል።

5/ የአዲስ አበባ ሕዝብ ብሶት፣ቁጣና ተቃውሞ ገንፍሎ ሊወጣ የተቃረበ ሱናሚ ይመስላል፤ይህንን የሕዝብ ተቃውሞ የፈራው የመንግሥት አካል ፣በተለይም የአዲስ አበባ አስተዳደር ለከተማዋ ሰላም በሚል ሽፋን ተጨማሪ 50,000 ፖሊስ ለመቅጠር በመንቀሳቀስ ላይ ነው።የሚገርመው ተቀጣሪው የአዲስ አበባ ከተማንም ሆነ የነዋሪውን ስነ ልቦና የማያውቅ፣በቋንቋ የማይግባባ ፣ከባለጊዜዎቹ ሰፈርና ጎሳ የተመለመለ መሆኑ ነው።ለከተማዋ የፖሊስ ጥበቃ ቢያስፈልግ ከነዋሪው ሕዝብ  መመልመል ተገቢ ነበር።ሕዝቡ እራሱ የራሱን ሰፈር ለመጠበቅ ብቃት ያለው መሆኑን ከሰላሳ ዓመት በፊት በቀበሌ በኩል ቢሆንም  አሳይቷል። አሁንም ቢሆን የአዲስ አበባ ወጣት ለዚህ ተግባር አያንስም።ድጋፍና ስልጠና ከተሰጠው እንኳንስ የተወለደበትን ከተማ ሌሎቹንም የኢትዮጵያ ከተሞች ሕዝብ ለማገልገል ችግር አይኖርበትም።የቋንቋ ችሎታውና ዘመናዊነቱ፣የከተማ ልጅ መሆኑ ለማህበረሰቡ ክብርና ፍቅር

እንዲላበስ አድርጎታል።በጎሳ ህሳቤ ያልታጠረና ያልተበከለ አይምሮ ባለቤት ስለሆነም ለችግሮች መፍትሔ ለመስጠት አይቸገርም።ዱላና ጥይት ለወራሪ ጠላት እንጂ  ለሕዝብ እንደማይመዘዝ በሚገባ ያውቃል።

ማጠቃለያ

የግፍ ዋንጫው ሞልቶ ይፈሳል። ጽንስ ከሆድ ውስጥ ተመዞ የሚጣልበትን ጭካኔ ባዩንበትና በሰማንበት ሰሞኑን ደግሞ የሰው ልጅ እንደ እንጨት በቁሙ ሲቃጠል ታዝበናል።ከባሌ  ህጻናት በማንነታቸው ታፍነው ለሽያጭ ቀርበው በክፍያ ምክንያት ስምምነት ላይ ሳይደረስ መጨናገፉን በማስረጃ ተመልክተናል

ሁሉም ያለቅሳል፤ተማሪውም አስተማሪውም ያለቅሳል፤ገበሬውም ነጋዴውም ያለቅሳል፤ወጣቱም አዛውንቱም ያለቅሳል፣ሴቱም ወንዱም ያለቅሳል፤ሃኪሙም በሽተኛውም ያለቅሳል፤ሠራተኛውም አሠሪውም ያለቅሳል፤ተከራዩም አከራዩም ያለቅሳል፤ሾፌሩም አውታንቲውም፣ተሳፋሪውም ያለቅሳል፤ ክርስቲያኑም ሙስሊሙም ያለቅሳል፤ሸማቹም ቸርቻሪውም ያለቅሳል፤ልጁም አዋቂውም ያለቅሳል፤ የሁሉም ጎሳ ተወላጅ ያለቅሳል።የማያለቅስ ቢኖር ሥልጣኑን የተቆጣጠረው ተረኛው ቡድንና አጃቢዎቹ ናቸው።

ደግመን ደጋግመን እንዳሳሰብነው የብልጽግና ፓርቲ የሚመራበት የጎሳ ፖለቲካ በችግር ላይ ችግር ፣ በቀውስ ላይ ቀውስ የሚፈጥር፣ሌቦች ተሰባስበው የሚዘርፉበት ስርዓት ባለቤት ስለሆነ መወገድ ይኖርበታል።ሕዝቡ ካለበት መከራ ለመላቀቅ፣ከወደፊቱም ውድቀት ለመዳን የግድ  የትግሉን አቅጣጫ የሚቀይስና የሚመራ ሕዝባዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ለስር ነቀል ለውጥ( Peoples coordinating committee for fundamental change))ነገ ዛሬ ሳይል ማቋቋም ይኖርበታል።በዚህ ኮሚቴ ውስጥ ለመካተትም

ሀ/በኢትዮጵያዊነቱ፣ በኢትዮጵያ አንድነትና በዳር ድንበሯ መከበር የሚያምን

ለ/የጎሳ ፖልቲካን የሚጠዬፍ፤ቋንቋ ተኮር የክልል አወቃቀርን የማይቀበል

ሐ/በፍትሕ ሥርዓት መስፈንና በዜጎች እኩልነት የሚያምን

መ/የባዕዳን መሣሪያና ጥገኛ ያልሆነ፣በራስ መተማመን ላይ የጸና አቋም ያለው ፍጹም አገር ወዳድ

በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚኖረው ከላይ በተጠቀሱት መሰባሰቢያ መርሆዎች የሚያምን ኢትዮጵያዊ ሁሉ በያለበት ኮሚቴውን ፈጥሮ እንዲንቀሳቀስ ጥሪ እናደርጋለን።ግንኙነቱን ለመጀመር በተቋቋመውበኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የግንኙነትና የስነጽሑፍ ክፍል የኢሜል አድራሻ አስተያዬታችሁን እንድትልኩልን በአክብሮት እንጠይቃለን።

የኢሜል አድራሻችን

Ethioandneteditorial1@gmail.com

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!